የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.18
ADDIS ABABA, 22nd December, 2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፮/፪ሺ፲ ዓ.ም

ለፍትሀዊ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የተጨማሪ ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.................................ገፅ ፲ሺ፶፱

**CONTENT**

Proclamation No.1066/2017

International Development Association Additional Financing Agreement for Financing the Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services Program Ratification Proclamation …………………page 1059

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፮/፪ሺ፲

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለፍትሐዊ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፬፻፴፩ ሚሊዮን ኤስ ዲ አር (አራት መቶ ሰላሳ አንድ ሚሊዮን ኤስ ዲ አር) ተጨማሪ ብድር የሚያስገኘው ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መስከረም ፲፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፮ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No.1066/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FANANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMWENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, an Additional Financing Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Democratic Republic of Ethiopia an Additional Loan amount of 431,000,000 Special Drawing Rights ( Four hundred thirty one million SDR) for financing the Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services program was signed in Addis Ababa on the 29th day of September, 2017;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 5th day of December, 2017;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

**፩.<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለፍትሀዊ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የተጨማሪ ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፮/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.የ<u>ስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መስከረም ፲፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የተጨማሪ ብድር ስምምነት ቁጥር 6131-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫.<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስልጣን</u>**

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፬፻፴፩ ሚሊዮን ኤስ ዲ አር (አራት መቶ ሰላሳ አንድ ሚሊዮን ኤስ ዲ አር) ተጨማሪ ብድር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከተወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW,THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the"International Development Association Additional Financing Agreement for Financing the Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services Program Ratification Proclamation No.1066/2017".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Number 6131-ET signed in Addis Ababa, on the 29th day of September, 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association, is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utlilization of the Loan amount of SDR 431, 000,000 Special Drawing Rights (four hundred thirty one million SDR) in accordance with the terms and conditions setforth in the financing Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this 22nd day of December, 2017**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**